# ደጅህን ዝጋ!

## ጸጋ ቃለ ሕይወት ቤተ ክርስቲያን

**ሕዳር 14፡ 2017 ዓ.ም.**

ኢሳ.26፡ 20

*ሕዝቤ ሆይ፥ ና ወደ ቤትህም ግባ፥ ደጅህን በኋላህ ዝጋ ቍጣ እስኪያልፍ ድረስ ጥቂት ጊዜ ተሸሸግ።*

በመጋቢ መርዓዊ ንጉሴ

# የኢሳይያስ ጥሪ

## ኢሳ.26:14

- አቤቱ፥ በመከራ ጊዜ ፈለጉህ፥ በገሰጽሃቸውም ጊዜ ልመናቸውን ወደ አንተ አፈሰሱ። የፀነሰች ሴት ለመውለድ ስትቀርብ እንደምትጨነቅና በምጥ እንደምትጮኽ፥ አቤቱ፥ እንዲሁ በፊትህ ሆነናል። እኛ ፀንሰናል ምጥም ይዞናል፥ ነፋስንም እንደምንወልድ ሆነናል፤ በምድርም ደኅንነት አላደረግነም፤ በዓለምም የሚኖሩ ይወድቃሉ። ሙታንህ ሕያዋን ይሆናሉ፥ ሬሳዎችም ይነሣሉ። በምድር የምትኖሩ ሆይ፥ ጠልህ የብርሃን ጠል ነውና፥ ምድርም ሙታንን ታወጣለችና ንቁ ዘምሩም። ሕዝቤ ሆይ፥ ና ወደ ቤትህም ግባ፥ ደጅህን በኋላህ ዝጋ ቍጣ እስኪያልፍ ድረስ ጥቂት ጊዜ ተሸሸግ።

# የነቢዩ ኢሳይያስ መልእክት፤

- የዚያ ዘመን የእስራኤላውያን ስጋት ምን ነበር

  አሦራውያን እያስፈራሯቸው ነበር

መፍትሔ

- ወደ ቤትህ ግባ
- ደጅህንም ከኋላህ ዝጋ
- ቁጣው እስኪያልፍ ድረስ ተሸሸግ

# በር በመዝጋት ከእግዚአብሔር ጋር ኅብረት ማድረግ፤

- ማንኛውም ወዳጅነት የጠበቀ ጊዜ መውሰድ ይፈልጋል
- እግዚአብሔርም፣ ከእርሱ ጋር ጥብቅ ኅብረት እንዲኖረን ይሻል
- መንፈሳዊ ፍሬ ልናፈራ የምንችለው፣ ከእግዚአብሔር ጋር ወዳጅነታችን በጠበቀ መጠን ነው

- *ዮሐ.15፡ ‹‹እኔ የወይን ግንድ ነኝ፤ . . . እናንተም ቅርንጫፎች ናችሁ፡ . . . ቅርንጫፍ በወይኑ ግንድ ባይኖር ፍሬ ሊያፈራ አይችልም፡*

# ከእግዚአብሔር ጋር ኅብረት ስናደርግ ፧

1. ማንነቱን እያወቅን እንሄዳለን
2. ባህርይውን ይበልጥ እንረዳለን

- እግዚአብሔርን ለማወቅና ባህርይውን ለመረዳት ደግሞ ከእርሱ ጋር የምናሳልፍበት በቂ ጊዜ ሊኖረን ይገባል

## ከእግዚአብሔር ጋር ያለን ኅብረት መገለጫዎች፡-

- ኅብረት ውስጥ ትውውቅ አለ
- ኅብረት ውስጥ አብሮነት አለ
- ኅብረት ውስጥ ተግባቦት አለ
- ኅብረት ውስጥ አጋርነት አለ

# ከክፉ ወዳጅነት ተጠበቁ

- ክፉ ወዳጅነት ከእግዚብሔር ጋር ያለንን ኅብረት ያስተጓጉላል

- 1ቆሮ.15፥33

*አትሳቱ፤ ክፉ ባልንጀርነት መልካሙን አመል ያጠፋል።*

- ምናልባት አንዳንድ እጅግ ጠቃሚ መስለው የሚታዩ ነገሮቻችን እጅግ የሚጎዱን ሊሆኑ ይችላሉ

# ስለ ወዳጅነት፣ የተነገሩ አባባሎች

- ከማን ጋር እንደምትውል ንገረኝና ማንነትህን እነግርሃለሁ

- ከአጋም የተጠጋ ቁልቋል ዕድሜ ልኩን ሲያለቅስ ይኖራል

- በሬ ከአራጁ ጋር ይውላል

# አጋም እና ቁልቋል





# በሬ ካራጁ



# ከእግዚብሔር ጋር ጥብቅ ወዳጅነት የምናደርገው

- እግዚአብሔርን በልዩ ልዩ መንገድ ስናመልከው ጊዜ እንደ ሰጠነው ይታወቃል፡ በዚሁ መሠረት ወዳጅነት፤

- ለቃሉ ጊዜ በመስጠት የሚገለጥ ነው
- ለጸሎትና ለፆም ጊዜ በመስጠት የሚገለጥ ነው
- ለአማኞች ጋር ኅብረት በማድረግ የሚገለጥ ነው
- ለአገልግሎት ጊዜ በመስጠት የሚገለጥ ነው

# ከእግዚአብሔር  ጋር ጽኑ ኅብረት ስናደርግ በራችንን መዝጋት አለብን

- *ማቴ.6፡6*

*አንተ ግን ስትጸልይ፥ ወደ እልፍኝህ ግባ መዝጊያህንም ዘግተህ በስውር ሳለው አባትህ ጸልይ፤ በስውር የሚያይ አባትህም በግልጥ ይከፍልሃል።*

ጸሎት፣፣

1. መግባት
2. መዝጋት
3. መጸለይ
4. መጠበቅ

# ከእግዚአብሔር ጋር ጽኑ ኅብረት ስናደርግ በራችንን መዝጋት አለብን

- *ማቴ.6፡6*

*አንተ ግን ስትጸልይ፥ ወደ እልፍኝህ ግባ መዝጊያህንም ዘግተህ በስውር ላለው አባትህ ጸልይ፤ በስውር የሚያይ አባትህም በግልጥ ይከፍልሃል።*

## እልፍኝን መዝጋት

- የውስጥ በርን መዝጋት
- የውጪ በርን መዝጋት

# የውጪው በር



- ማንኛውም የተለመደው ዓይነት በር ሊሆን ይችላል

# የውጪው በር

- እንደ ስልክና ከስልክ ጋር የተያያዙ ነገሮችም ሊሆኑ ይችላሉ



# ስልካችን ሁለነገራችን ግን ተግዳሮታችን!

- የዚህ ዘመን አማኞች እልፍኞቻችንን ዘግተን /አሳባችንን ሰብስበን/ በአምላካችን ፊት እንዳንሆን ከሚፈታተኑን ነገሮች አንዱ ስልካችን ነው

- በዛሬው ትምህርት ከስልካችን ጋር ተያይዞ የገጠመንን የትኩረት ማጣት ፈተና ለመወጣት የሚያስችሉ ተግባራዊ ጉዳዮች ላይ እናተኩራለን

# ለመሆኑ በዚህ ሰዓት ስንቶቻችን ስልካችን ዘግተናል?



# ቀላል የክፍል ሥራ ጥያቄ

- ምናልባት

‹‹ክልኬን ከምዘጋ ጉባዔውን ትቼ መሄድ ይቀለኛል››

የሚል አንድ ሰው እዚህ ጉባዔ ተቀምጦ ይሆን፣

## ማስተባበል ያልቻልነው ሐቅ

# ስልካችን ከእግዚአብሐር ጋር ያለንን ወዳጅነት እየፈተነው ነው

# ስልካችን ሁለነገራችን

- ይህ ዘመን ይዞልን ከመጣው በርካታ ቴክኖሎጂዎች አንዱ ስልካችን ነው

- ስልካችን ሁለነገራችን ነው

- ስለዚህ ከስልክ መለየት የማይታሰብ ነው

# ስልክ፣ መነጋገሪያ ብቻ ሳይሆን፣

- ባንካችን፣
- ካሜራችን፣
- አልበማችን፣
- ካልኩሌተራችን፣
- መብራታችን፣
- ቴሌቪዥናችን
- ጤንነታችንን መከታተያችን፣ . . .

# ስልካችን ሁለነገራችን

- በዚህ ቀን ከስልካችን እና በስልካችን ውስጥ ካሉ ነገሮች አንጻር ያለን ቆይታ እንመረምራለን

- በዚህም ከእግዚአብሔር ጋር ላለን ኅብረት ስልካችን እንቅፋት እንዳይሆንብን ገደብ ለማበጀት እንወስናለን ብዬ እጠብቃለሁ

- በተጨማሪም ስልካችንንና ከስልካችን ውስጥ ያሉ ነገሮችን እንዴት ለመልካም ተግባር መጠቀም እንደምንችል እናያለን

## ማሳሰቢያ፡

- ለዚህ መልእክቴ በቅርብ የታተሙ ሁለት መጽሐፍትን በዋነኝነት በግብአትነት ተጠቅሜአለሁ

መልእክቱን በሚገባ ለመረዳት በዋነኝነት የአሳየኸኝ ለገሰን ‹‹የመጻተኛው ስልክ››የተሰኘው መጽሐፍ በእጃችሁ እንድታገኙት ጥረት አድርጉናል

# የመጻተኛው ስልክ



# አንዳንድ ዝንተዓለም የኖሩ የሚመስሉ ነገሮች፣ ዕድሜአቸው አጭር ጊዜ ነው

አንዳንድ ነገሮች ዘመናቸው እጅግ በጣም አጭር ጊዜ ቢሆንም ለዝንተ ዓለም የኖሩ ያህል ዓለምን ተቆጣጥረውታል

ለምሳሌ ስልክ ዓለም ከተፈጠረ ጀምሮ አብሮን የኖረ መስሎ ቢታየንም ዘመኑ ግን አጭር ነው

# ፈጣኑ የቴክኖሎጂ ዕድገት እና የአማኞች ፈተና

## ቴክኖሎጂ ባለፉት መቶ ዓመታት በፍጥነት እያደገ ነው

- ዕድገቱ እመርታ ምን ያህል እንደ ሆነ ለማሰብ እንኳ ይከብዳል

- የአምስት ሳንቲሟ ታምራዊ እመርታ

*በአንድ ጊዜ 100 ሺ ብር ልስጥህ ወይስ ከአምስት ሳንቲም ጀምሬ ለ30 ቀን ልስጥህ*

## የሠላሳኛው ቀን ተዓምር

# 26,843,546

# ብር

**የዓለም ፈጣን ዕድገት፣ ወደ ጥፋቷ የመቻኮሏ ምልክት ነው!**




## ለምሳሌ ሞባይል ስልክ ኢትዮጵያ ውስጥ ስንት ዓመ ነው?



# ሞባይል ስልክ ኢትዮጵያ ውስጥ ዘመኑ ስንት ነው?

- ለመጀመሪያ ጊዜ ኢትዮጵያ ውስጥ ሞባይል ጥቅም ላይ የዋለው 1992 ዓ.ም አካባቢ ነው

- የዚያን ጊዜ ሞባይል መያዝ የባለጠግነት ምልክት ተደርጎ ይወሰድ ነበር

- በዛሬው ጊዜ ግን ሞባይል የሌለው ሰው ማግኘት አይቻልም

# ይህ ስልክ የሰፈር ሰዎች ሁሉ ይጠቀሙበት ነበር



# የዓለም አስገራሚው የቴክኖሎጂ እመርታ ዕብነት

- የገመድ ስልክ 1876
- ሬድዮ 1895
- ቴሌቪዥን 1927 (በኢትዮጵያ 1954 ዓ.ም)
- ኮምፒዩተር ለሕዝብ መቅረብ የጀመረው ከ1970 በኋላ ነው

# ይህ ቲቪ የጎረቤት ሰው ሁሉ ተጠራርቶ ማታ ማታ ይመለከተው ነበር



# የጎረቤት ልጆች ማታ ማታ ተሰብስበው የሚያዩት



# ይህ ቴፕ ሪከርደር ለብዙዎቻችን ባለ ውለታ ነው

ለምሳሌ፣ የመጋቢ ተስፋዬ ጋቢሶ የመጀመሪያ የመዝሙር ካሴቶች ወደ አማኞች የደረሱት በዚህ ዓይነት ቴፕ ሪከርደር ተቀርጸው ነበር



# ኮምፒዩተር ለሕዝብ መቅረብ የጀመረው ከ1970 በኋላ ነው



# ፈጣኑ የቴክኖሎጂ ዕድገት እና የአማኞች ፈተና

- ኢንተርኔት የተጀመረው 1990

- ዲጅታል ስልክ የተጀመረው 2003 <u>ብላክቤርይ</u> የተባለ ስልክ ሲሠራ ነው



# አይፎን የመጀመሪያውን ስማርት ፎን የሠራው በ2007 ነው



# በዛሬው ጊዜ



- ከ5 ሚሊዮን በላይ የሞባይል ተጠቃሚዎች አሉ
- ከ4 ቢሊዮን በላይ የኢንተርኔት ተጠቃሚዎች አሉ
- ከ3 ቢሊዮን በላይ የማህበራዊ ሚድያ ተጠቃሚ ናቸው

# የማኅበራዊ ሚድያዎች አጀማማር

- **በ2004** ማርክ ዙገርበርግና ጓደኞቹ ለሐርቫርድ ዩንቨርሲቲ ተማሪዎች እርስ በርስ ለመገናኘት ብቻ የሚያገለግል ቴክኖሎጂ ፈጠሩ
- **በ2006** እነዚሁ ወጣቶች የትኛውም የኢንተርኔት ተጠቃሚ አገልገሎቱን እንዲያገኝ አስፋፋት
- **2007** አይፎን ስማርት ፎን መጀመሩን ተከትሎ ማንኛውም ሰው በእጅ ስልኩ ፌስ ቡክ መጠቀም እንዲችል ዕድል ተፈጠረ
- **በ2018** በተደረገ ጥናት ከ2.6 ቢሊዮን በላይ የፌስ ቡክ ተጠቃሚ ነው/30% / የዓለም ሕዝብ ማለት ነው


facebook
facebook
facebook



# ፌስ ቡክ ጊዜው እያለፈበት ነው!




- በዚህ ዘመን ፌስ ቡክ የሽማግሌዎች እንደ ሆነ ነው የሚታሰበው

- የመጻተኛው ስልክ መቅድም የጻፈው ሰው ምስክርነት፣



# ከፌስ ቡክ ቀጥሎ የመጡ የማኅበራዊ ሚድያ መተግበራረያዎች

- በ2005 ዩቲዩብ
- በ2006 ቲዩተር
- በ2010 ኢንስታግራም
- 2012 ስናፕ ቻት
- 2013 ቴሌግራም
- 2016 ቲክቶክ

# ስልቹና ትዕግሥት አልባ ማኅበረሰብ

- በአሁኑ ጊዜ ማኅበረሰባችን ትዕግሥት የለሽ ሆኗል
- በዚህ ምክንያት ማኅበራዊ ሚድያው አጫጭርና ጥልቀት በሌላቸው ጉዳዮች ላይ የሚያጠነጥን ሆኗል
- ለምሳሌ የቲክቶክ አጫጭር ቪዲዮዎችን በዋቢነት መጥቀስ እንችላለን

# ቴክኖሎጂ ሁሉ ክፉ ወይም መጥፎ ግን አይደለም

| | |
| --- | --- |
| የ ጥበብ | የዓለም ጥበብ |

ማንኛውንም ነገር ለእግዚአብሔር  ክብር መዋጀት ይገባል!

# ጥበብ ሁሉ የተሰጠው ከእግዚብሔር ነው

- ሁሉንም ዓይነት ጥበብ ለሰው ልጅ የሰጠ እግዚብሔር  ነው
- የትኛውንም ዓይነት ጥበብ ለእግዚአብሔር ክብርና ለወንጌል አገልግሎት ልናውለው እንችላለን
- ሰይጣን ደግሞ ጥበብን ለክፋቱ ይጠቀምበታል
- የእኛ ኃላፊነት ጥበብን ዋጅተን ለጌታ ክብር ማዋል ነው

# ለጢሮስ ንጉሥ የተነገረ ሙሾ

## ሕዝ 28፥12

*የሰው ልጅ ሆይ፥ በጢሮስ ንጉሥ ላይ ሙሾ አሞሽተህ እንዲህ በለው።*

- ይህ ሙሾ የተሞሸው ለጢሮስ ንጉሥ ነው ቢልም ገለጣው ግን ለሠይጣን እንደ ሆነ ነው የሚታመነው፡፡

# ሰይጣን . . .

- ለጥበቡ ወደር አልነበረውም

  *ጥበብን የተሞላህ ውበትህም የተፈጸመ መደምደሚያ አንተ ነህ*

- በከበረ ስፍራ ይኖር ነበረ

  *በ ገነት በዔድን ነበርህ፤*

  *በተቀደሰው በ ተራራ ላይ አኖርሁህ፤*

  *በእሳት ድንጋዮች መካከል ተመላለስህ።*

# ሰይጣን . . .

- **አለባበሱ ፍጹም የተለየ ነበር**

  *የከበረ ዕንቍስ ሁሉ፥ ሰርድዮን፥ ቶጳዝዮን፥ አልማዝ፥ ቢረሌ፥ መረግድ፥ ኢያስጲድ፥ ሰንፔር፥ በሉር፥ የሚያብረቀርቅ ዕንቍ፥ ወርቅ፥ ልብስህ ነበረ፤*

- **የተለየ የሙዚቃ ችሎታ ነበረው**

  *የከበሮህና የእንቢልታህ ሥራ በአንተ ዘንድ ነበረ፤*

# ሰይጣን . . .

**ለጥበብ የተቀባ ነበር**

*በተፈጠርህበት ቀን ተዘጋጅተው ነበር።*

*አንተ ለትጋርድ የተቀባህ ኪሩብ ነበርህ፡፡*

*ከተፈጠርህበት ቀን ጀምረህ በደል እስኪገኝብህ ድረስ በመንገድህ ፍጹም ነበርህ።*

# የሰይጣን ትዕቢትና ኲራት፤ ጥበብህን አረከሳት!

- <u>**ውበቱ ያመጣበት ትዕቢት**</u>

  *በውበትህ ምክንያት ልብህ ኰርቶአል፤*

- <u>**የእርሱ ያልሆነ ክብርን መሻቱ**</u>

  *ከክብርህ የተነሣ ጥበብህን አረከስህ፤*

**ለመቅደሱ የነበረውን አገልግሎት በዚህ ዓለም ንግድ አረከሰ**

# ጥበብን በማርከሱ፤ የእግዚአብሔር ቅጣት

*ስለዚህ እንደ ርኩስ ነገር ከተራራ ጣልሁህ፤*

*የምትጋርድ ኪሩብ ሆይ፥ ከእሳት ድንጋዮች መካከል አጠፋሁህ።*

*በምድር ላይ ጣልሁህ ያዩህም ዘንድ በነገሥታት ፊት ሰጠሁህ።*

ሰው የሰጠውን ጥበብ በአግባብ ካልተጠቀመ የተሰጠው ነገር መልሶ ሊያጠፋው ይችላል

## እሳትን ከውስጥህ አውጥቻለሁ እርስዋም በልታሃለች

በሚያዩህም ሁሉ ፊት በምድር ላይ አመድ አድርጌሃለሁ።

በአሕዛብም ውስጥ የሚያውቁህ ሁሉ ይደነቁብሃል፤

አንተም ለድንጋጤ ሆነሃል፥ እስከ ዘላለምም አትገኝም፡፡

# በየትኛውም ዘመን ቢሆን፣
# ለእግዚአብሔር ክብር ያልዋለ ጥበብ አደገኛ ነው

- ማኅበራዊ ሚድያን ጨምሮ በጥበብ ያልተገራ ነገር ከጥቅሙ ጉዳቱ እንደሚያመዝን የተረጋገጠ እውነት ነው
- ከዚህም በላይ ሌሎች ዘርፈ ብዙ ጉዳቶችን ሊያስከትል እንደሚችል መረዳት አለብን
- ከዚህ ቀጥሎ እነዚህ የጎንዮሽ ጉዳቶችን ነቅሰን እናያለን

# የማኅበራዊ ሚድያ አደገኛነት እና ልዩነት ከፕሪንት ሚድያ አንጻር

የተጻፈ ነገር ስናነብ አእምሮአችን ብዙ ማሰብ ይችላል

- ምስል፣
- ቦታ፣
- ድምፅ
- ጊዜና ወቅት ይከሰታል

# የማኅበራዊ ሚድያ አደገኛነት እና ልዩነት ከኤሌክትሮኒክ ሚድያ አንጻር

- ሬድዮ ከሆነ ድምፁን ብቻ ነው የምንሰማው
- ቴሌቪዥን ከሆነ ደግሞ ምስሉንም እናያለን

- ሬድዮ ስንሰማ ቴሌቪዥን ስናይ ከራሳችን ጋር ጊዜ ወስደን ለማሰላሰል ዕድል እናገኛለን

- ማኅበራዊ ሚድያው ግን ከማሰላሰላችን በፊት ግብረ መልስ የመስጠት ዕድል ስለሚሰጠን የማሰላሰያ ዕድላችንን ይነፍገናል

# ከዚህ አንጻር ማኅበራዊው ሚድያ ያስከተለው ጉዳት ምንድነው?

ብዙዎችን አላዋቂዎች አዋቂ ያስመሰላቸው ይህ ዓይነቱን ዕድል ያለ ከልካይ ማግኘታቸው ነው

- አርቆ የማያስብ
- ስሜታዊ
- ጽንፈኛ
- ሱሰኛ

ማኅበረሰብ ለመፈጠር ምክንያት ሆኗል

# የማኅበራዊ
# ሚዲያ
# ሱስ

# የማኅበራዊ ሚድያው ሱስነት

- በ2023 በተደረገ ጥናት ከ2.3 ቢሊዮን የማኅበራዊ ሚድያ ተጠቃሚዎች መኻል 330 ሚሊዮኑ ሱሰኞች መሆናቸው ተረጋግጧል
- በአሁኑ ጊዜ የሱሰኛው ቁጥር በየቀኑ እየጨመረ ነው

# ሱስ ምንድን ነው?

- አንድ ነገር ስህተት መሆኑን እያወቅን እንኳ መላቀቅ የሚቸግረን ነገር ከሆነ፣
- አእምሮአችንን ፈጽሞ የሚቆጣጠረን ነገር ከሆነ፣
- በተደጋጋሚ ለማድረግ  የምንፈልገው ነገር ከሆነ፣
- ስናጣው ከፍተኛ ድብርት የሚሰማን ከሆነ

# ሁለት ዓይነት ሱስ አለ



# ሁለት ዓይነት ሱስ አለ

## የንጥረ ነገር ሱስ /substance addiction

- የዕጽ ሱስ
- የሲጃራ ሱስ
- የጫት ሱስ
- የመጠጥ ሱስ
- የጣፋጭ ምግቦች ሱስ

# ሁለት ዓይነት ሱስ አለ

## የሂደት ሱስ /process addiction

- የሥራ ሱስ
- የፊልም ሱስ
- የስፖርት ሱስ
- የልመና ራሱ ሱስ
- የስልክ ሱስ
- የማኅበራዊ ሚድያ ሱስ

# ሱስ ቀላል ነገር አይደለም

## ለምሳሌ የልመና ሱስ ያለበት ሰው መልስ

- የልመና ሱስ ያለበት ሰው ሎተሪ ቢደርስህ ምን ታደርጋለህ ቢባል፤፤ መኪና ገዝቼ ከአገር አገር እየዞርኩ እለምን ነበር ብሎ መልሷል

# የስልክ እና ማኅበራዊው ሚድያ ሱስ



# የስልክ እና ማኅበራዊው ሚድያ ሱስ

- የማኅበራዊ ሚድያ ሱስ በአንጎል ላይ የሚያስከትለው ለውጥ አደገኛ ዕፅ ከሚወስዱ ሰዎች ጋራ ተመሳሳይ ነው
- የአደገኛ ዕፅ ሱሰኞች፣ ስለሚወስዱት ንጥረ ነገር ገና ማሰብ ሲጀምሩ፣ ዶፓሚን ("Dopamine") የሚባል የደስታን ስሜት ማእከል የሆነ ቅመም ወይም ኬሚካል (hormone) በአእምሮአቸው ውስጥ መረጨት ይጀምራል።
- ይህ ቅመም የተለየ ንቃት የሚሰጣቸው ሲሆን፣ ልማዱ ከተጓደለ ለድባቴና ለአእምሮ ጭንቀት አሳልፎ ይሰጣቸዋል።

# የስልክ እና ማኅበራዊው ሚድያ ሱስ

- ከማኅበራዊ ሚድያ ባሕርያዊ ሱስም ከዶፓሚን መመንጨት ጋራ ይያያዛል
- በዛሬው ጊዜ ብዙ ሰው ስልኩ አብሮት ከሌለ ባዶነትና ድብርት ይሰማዋል
- ብዙ ወጣቶች ስልካቸውን ወይም ታብሌታቸውን ከሚያጡ እናት አባታቸውን ቢያጡ እንደሚመርጡ ጥናቶች ያሳያሉ

# የስልክ እና ማኅበራዊው ሚድያ ሱስ




- ብዙ ጊዜ በማኅበራዊ ሚድያ ሱስ የተያዘ ሰው የማገናዘብ አቅሙ ደካማ ከመሆኑም በላይ ለጭፍን አመለካከቶች ተጋላጭ ይሆናል፡፡

# የስልክ እና ማኅበራዊው ሚድያ ሱስ

- እያንዳንዱ ሰው በቀን **2500** ጊዜ በላይ ስልኩን ይነካል
- ይህንን ተግባር ግንባራችንን ለመንካት ብናውለው ግንባራችን ይበልዝ ነበር
- በአፍሪካ በአማካኝ አንድ ሰው **ለ3 ሰዓት** ያህል በማኅበራዊ ሚድያ ላይ ጊዜ ያጠፋል

# አስደንጋጩ ነገር



# አስደንጋጩ ነገር

- አስደንጋጩ ነገር የእነዚህ ሚዲያዎች ሱስ አስያዥነት ሳይታሰብበት የመጣ የጎንዮሽ ውጤት ሳይሆን በሚዲያዎቹ ፈጣሪዎች በጥንቃቄ የተነደፈ መሆኑ ነው።

- ሚዲያዎቹ፣ የገጾቻቸውን ንድፍ ሲሠሩ፣ ተጠቃሚው ሰው በስልኩ ስሌዳ ላይ ለረዥም ሰዓታት እንዲቆይ ማድረግን ታሳቢ አድርገው ነው።

# ለምን?



# ነገሩ ከንግድ እና ትርፍ ጋር የተያያዘ ስለሆነ ነው

- ሚዲያዎቹ ትርፋማ የሚሆኑት የሚሊዮኖችን ትኩረት መቈጣጠርና ማሳተፍ ከቻሉ በመሆኑ፣ ተጠቃሚዎች በቀላሉ ለመላቀቅ እንዲከብዳቸው አድርገው ይሠሯቸዋል፤

- <u>ይህንንም ንድፍ አውጪዎቹ “የአዕምሮ ጠለፋ” (brain hacking) በማለት ይጠሩታል።</u>

# ነፃ አገልግሎት አይደለም

- የቴክኖሎጂ ኩባንያዎች አገልግሎቶቻቸውን በነጻ የሚሰጡን ከመሰለን ሳስተናል!!

- በእነርሱ ዘንድ እንደ ተገልጋይ ሳይሆን እንደሚሸጥ ምርት ነን

- ማኅበራዊ ሚዲያዎች ስለእኛ የሰለሉትን መረጃ ለማስታወቂያ ድርጅቶች ይሸጣሉ፤

# ነፃ አገልግሎት እያገኘን አይደለም

- ድርጅቶቹም ፍላጎታችንን መሠረት ያደረጉ ምርቶቻቸውን በገጾቹ ላይ ያስተዋውቃሉ።
- በዚህም ሚዲያዎቹ በበርካታ ሚሊዮን ዶላሮች ገቢ ያገኛሉ።
- በዲጂታሉ ዓለም "ለምታገኘው አገልግሎት ወይም ምርት ምንም ካልከፈልክ፣ አንተ ራስህ ምርት ነህ ማለት ነው" የሚባለው በዚህ ምክንያት ነው።

# ረቂቁ ቀመር

- የዘርፉ ባለሙያዎች፣ የገጾቻቸውን ኀብኘዎች ፍላጎት አጥንቶ ለማወቅ የረቀቀ ቀመር ይጠቀማሉ

- ቀመሩም፣ ስልተ ቀመር (ወይም “Algorithm”) ይባላል።

- ተጠቃሚዎች ምን ዐይነት ይዘቶችን ማየት፣ መስማትና ማንበብ እንደሚወድዱ በዚህ ሰው ሠራሽ የማገናዘብ ችሎታ ባለው ቀመር ይሰልላሉ።

# የስልተ ቀመሩ አሠራር እንዲህ ነው፤

- ሚዲያዎቹን አንድ ጊዜ የጎበኘ ሰው፣ ጊዜ ሰጥቶ በተመስጦ የተከታተለው ልጥፍ ምን ዐይነት እንደ ሆነ ይለያል
- ከዚያም ተመሳሳይ ይዘት ያለው ልጥፍ ለተጠቃሚው በተደጋጋሚ እንዲቀርብለት ይደረጋል
- በተጨማሪም ጎብኚው <u>በግብረ መልስ መስጫ ቍልፎች (feedback buttons) አማካይነት መውደዱንና አድናቆቱን መግለጡን በቀመሩ ይሰለላል</u>

## የስልተ ቀመሩ አሠራር እንዲህ ነው፤

# ብዙ ጊዜ የምንወደው ምን ዐይነት ይዘት ያለውን ልጥፍ እንደሆነ የሚደርስበት፣ ራሳችን በምናደርገው ተሳትፎ ነው

# የስልተ ቀመሩ አሠራር እንዲህ ነው፤

ለምሳሌ፡-የስፖርት፣ የፖለቲካ፣ የፊልምና. . . የመሳሰለው ዝንባሌአችን በቀመሩ በኩል ይጠናል፣ ይሰለላል

- ምን ዓይነት ስፖርት ትወዳለህ?
- የየቱ ቡድን ደጋፊ ነህ?
- ምን ዓይነት ቋንቋ ተናጋሪ ነህ?
- የየቱ የፖለቲካ ፖለቲካ ደጋፊ ነህ?
- መዝሙር ነው የምትሰማው ወይስ ዘፈን? ወ.ዘ.ተ. . .

# ቴክኖሎጂው ከዚያም በላይ አልፎ ሄዷልም ይባላል

## ከዚህም አልፎ

- ስንስቅ፣
- ስንናደድ፣
- ስናደንቅ
- ስሜታችንን አንብቦ የሚለይ ሥርዓት አለው

- ብዙ ሰዎች በስልኮቻቸውና በማኅበራዊ ሚዲያ ሱስ የተያዙበት በዚህ ምክንያት ነው

# የደካማ ጎናችን ሰላይ

- ሰው በመሆናችን ምክንያት እያንዳንዳችን ደካማ ጎኖች አሉን

- እያንዳንዳችን በግላችን ብንፈተሽ የሆነ ደካማ ጎን ይኖረናል

- ሰይጣን ሁል ጊዜ እነዚህን ደካማ ጎኖቻችንን ያጠናል

# የደካማ ጎናችን ሰላይ

- እነዚህ የዘርፉ ባለሞያዎች የሰውን ደካማ ጎን በማጥናት ይተጋሉ

- ከደካማ ጎናች መኻል ዋና ዋነዎቹ ደካማ ጎናችን

- አሳየኸኝ ለገሰ በመጽሐፉ አራቱን ደካማ ጎኖቻችንን አሳይቶናል

# የሰው ደካማ ጎን ምንድን ነው?

- ፩ኛ፡ ሰዎች ስለ እኛ ምን እንደሚሉ ወይም ምን እንደሚያስቡ የማወቅ ጉጉት

- ማኅበራዊ ሚዲያዎች ሲጠነሰሱ፣ የወዳጆችን ውሎና ዐዳዲስ ገጠመኞች ለመመልከት ከማስቻል ያለፈ አገልግሎት አልነበራቸውም።
- በኋላ ላይ ግን እንደ፣ "መውደድ (Like)"፣ "አስተያየት (Comment)" እና " ማጋራት (Share)" ያሉትን የግብረ መልስ መስጫ ቁልፎችን ጨምረው መጡ።

# የመወደድ (Like)”፣ “የአስተያየት (Comment)” እና “የማጋራት (Share)” ሱስ

- ከሰው ክብርና መወደድን የመሻት ሱስ
- ክብርና መወደድን የመሻት ሱስ ልክ እንደ ዕፅ ሱስ ነው፡፡ እንዲህ ዓይነቱ ክብር ስናገኘው ደስ ይለናል፡፡
- በተደጋጋሚ ካላገኘነው ደግሞ ድብርት ውስጥ ይጥለናል፡፡

# እነዚህ ነገሮች የበለጠ ሱሰኞች ያደርጉናል



ሱሰኛ ከሆንን ላይክ እና ኮሜንት ስናገኝ የምንደሰተውን
ያህል ሲጠፋ ደግሞ እናዝናለን



# 2ኛ፡ በዙሪያችንና በዓለማችን እየሆነ ያለውን ዐዲስ ነገር በየጊዜው የመስማት ጉጉት

- ወቅታዊ ኹነቶችን የመስማትና ከሚናፈሰው ወቅታዊ መረጃ ያለ መጉደል የማይነጥፍ ሰብኣዊ ፍላጎት አለን።

- ማኅበራዊ ሚዲያዎች ይህን ፍላጎታችንን አገናዝበው ነው የመጡት

- ስለዚህ በየዕለቱ ከአራቱም የዓለም ማእዘናት ትኩስ ወሬዎች በእጅ ስልኮቻችን በየአድራሻችን እንዲደርሱን አድርገዋል።

# ዐዲስ ነገር የመስማት ጉጉት

- አዲስ ዜና መስማት መጥፎ ላይሆን ይችላል፡፡
- የወሬ ሱሰኛ መሆን ግን አደጋ አለው
- ከምንም በላይ ግን ማለዳ ተነሥቶ ከጌታ ድምፅ መስማት ይሻላል

- *ምናልባት በማለዳ የምንሰማው ዜና ሕይወታችንን ሊያተርፍ ይችላል*

# ወሬኛዋ ኤሊ


THE
Talkative
TURTLE
Retold by Chitra Soundar
Illustrated by Nimisha Saikia
Read and Colour Activity
PANCHATANTRA
SCHOLASTIC

# ወሬኛዋ ኤሊ



# 3ኛ የስሜት ጫና ከሚፈጥሩብን የተለያዩ ነገሮች ዘወር የማለት ፍላጎት

- በውጥረት ስሜትና በሕይወት ትግል ውስጥ በምናልፍበት ጊዜ፣ ካለንበት ሁኔታ ጊዜያዊ እፎይታ ለማግኘት የመፈለግና ተዝናኖትን የመሻት ዝንባሌ ይኖረናል።
- የብቸኛነት ስሜት፣
- የሥራና የትምህርት ጫና፣
- ግጭት፣ የጥፋተኝነት ስሜት፣
- ሕመምና
- ሌሎችንም ልዩ ልዩ ፈታኝ ሁኔታዎቻችንን፣
- ለጥቂት ለመርሳትና አእምሮአችንን ከጫና ለመገላገል መደበቂያ እንፈልጋለን።

# 4፡ የማኅበራዊ ሚዲያ ግንኙነትን የማቋረጥ ፍራቻ

- ከማኅበራዊ ሚድያው ጋር ያለን ግንኙነት በሱስ ደረጃ ከደረሰ በኋላ መለየት ከባድ ነው

- በዲጅታሉ ዘመን፣ ከማኅበራዊ ሚዲያ የትስስር ገጾች ለጊዜውም ቢሆን ገለል ማለት ይህን የሚያስጨንቅ የመገለል ስሜት ይጋብዛል።

- በተለይ በዐሥራዎቹ የዕድሜ ክልል ያሉ ወጣቶች የዚህ ጫና ሰለባዎች ናቸው

- **አየሩ ላይ መቆየት መልእክትን በቀላሉ ለማድረስ ተመራጭ ሊሆን ይችላል**

# እንደ ማኅበረሰብ አደጋ ላይ ነን



# ችግሩ ቀላል አይደለም

## ችግሩ ሕመም ሆኖ የማገገሚያ ማእከላት ተከፍተዋል

- በአሁኑ ጊዜ ባደጉት አገራት፣ የጉዳዩን አሳሳቢነት በመረዳት በርካታ የበይነ መረብ ሱስ ማገገሚያ ማዕከሎችን ከፍተው አገልግሎት እየሰጡ ነው።
- ለዚህም እንደ አሜሪካ፣ ቻይና፣ ደቡብ ኮሪያ ያሉት ግንባር ቀደም ተጠቃሽ ናቸው።
- በተለይ፣ በዜጎች የበይነ መረብ ተጠቃሚ ቁጥር መሪ የሆነቻው ኮሪያ፣ **ከ140 በላይ ከክፍያ ነጻ አገልግሎት የሚሰጡ የማገገሚያ ማዕከላት አሏት፤**
- በ100 ሆስፒታሎችም ተመሳሳይ አገልግሎት ትሰጣለች

# የማኅበራዊ ሚድያዎች ተጽእኖ



# የማኅበራዊ ሚድያዎች ተጽእኖ

- የማኅበራዊ ሚድያ ገጾች የዓለምን አኗኗርና አስተሳሰብ ሙሉ ለሙሉ ቀይረውታል
- በአሁኑ ጊዜ በርካታ ቤተሰቦች የኅብረት ጊዜ የላቸውም
- ቤተሰባዊ መስተጋብሩ ከጊዜ ወደ ጊዜ እየተናጋ ነው
- ልጆችና ወላጆች ተራርቀዋል

# ችግሩ ቀላል አይደለም

- የስልክ ሱሰኞች፣ በአካል አብረው ቢሆኑም በነፍስ ግን አብረው አይደሉም፡፡
- ይህም ነገር የማኅበራዊ ግንኙነት ቀውስ ያመጣል
- የሚያሳዝነው ብዙዎች ሱሰኛ መሆናቸውን አያውቁም



# ሱሰኛ ስላለመሆናችን ምን ያህል እርግጠኞች ነን?

- በዕውቀት ያልተገራ፣ በሱስ ደረጃ ያለ የማኅበራዊ ሚዲያ አጠቃቀም፣ በግልና ማኅበራዊ ሕይወታችን ላይ የሚያስከትለው አሉታዊ መዘዝ ቀላል አይደለም።

- ዲጅታል መሣሪያዎች ባልተገባ ሁኔታ እንዳይሰለጥኑበትና የሂደት ሱስ እንዳይተክሉበት በመቈጣጠሩ ረገድ የአንበሳውን ድርሻ መውሰድ ያለበት ተጠቃሚው ራሱ ነው።

# የማኅበራዊ ሚድያ ሱስ አፍራሽ ነው



# ከሱስ መላቀቅ ቀላል አይደለም

- በማኅበራዊ ሚድያ ሱስ የተያዘ ሰው ከሱሱ ለመውጣት ቀላል አይሆንለትም፡፡

- ምናልባትም መለኮታዊ ጣልቃ ገብነት ያስፈልገው ይሆናል፡፡

- ምክንያቱም ማኅበራዊ ሚድያው ሲሠራ በረቂቅ ቀመር ተሰልቶ በመሆኑ ነው

# ከሱስ መላቀቅ ቀላል አይደለም



# የማኅበራዊ ሚድያው ሱስ ዋና ዋና ጉዳቶች

## አእምሮአችንን ይጎዳል

- አእምሮአዊና አካላዊ ጉዳቶችን ሊያስከትል ይችላል፣
- አጥፊ ባሕርያትን እንድናጎለብትም ሊያደርገን ይችላል።
- የሥነ ባሕርይና የሥነ ልቡና ባለሙያዎች እንደሚነግሩን፣ በዲጅታል መሣሪያዎች ሱስ መያዝ የአእምሮ ዕድገትና የመማር ክህሎትን ያቀጭጫል።
- ለድባቴና ለአእምሮ ጭንቀት ተጋላጭ ያደርጋል።

# የማኅበራዊ ሚድያው ሱስ ዋና ዋና ጉዳቶች

## ምርታማነትን ይጎዳል

- በስልኮች ላይ በሚባክኑ ጊዜያት ምክንያት የሥራ ፍሬያማነትን ይገድባል።
- ምሳሌ፡

በቀን ስንት ሰዓት ሥራ ላይ እናሳልፋለን?

የኢትዮጵያውያን የሥራ ባህልና የጊዜ አጠቃቀም



# የማኅበራዊ ሚድያው ሱስ ዋና ዋና ጉዳቶች

**በዕውቀት ያልተያዘ የማኅበራዊ ሚዲያ አጠቃቀም**

- ማኅበራዊ ገመዶን ይበጣጥሳል፤
- ትዳርን አደጋ ላይ ይጥላል
- ወደ ጾታዊና ወሲባዊ ምስቅልቅል ውስጥ ይከታል
- ወጣቶቻችን ራሳቸውን ለመቀበል የሚቸገሩና በማንነት ቀውስ ውስጥ የተዘፈቁ እንዲሆኑ ያደርጋል
- ውጥረቱን መቋቋም ሲሳናቸው ራሳቸውን እስከ ማጥፋት ሊደርሱ ይችላሉ፡፡

# የቀድሞ ዘመን እሴቶች እና ይህ የማኅበራዊ ሚድያ ዘመን ንጽጽር



# የቀድሞ ዘመን እሴቶች እና ይህ የማኅበራዊ ሚድያ ዘመን ንጽጽር



# የማኅበራዊ ሚድያው ሱስ ዋና ዋና ጉዳቶች

## እንደ ወንጌል አማኝነታችን ስናስብ

- አደጋው ሥነ ልቡናዊና ውጫዊ ከመሆን ባለፈ መንፈሳዊም ጭምር መሆኑን እንገነዘባለን።

- አንዳንዴም የዲጅታል ቴክኖሎጂዎቻችን ወደ ጣዖትነት ሊቀየሩብን የሚችሉበት አጋጣሚ አለ

# የማኅበራዊ ሚድያው ሱስ ዋና ዋና ጉዳቶች

## ከሚድያው ተጽእኖ የተነሣ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ አማኞች

- ትኩረት የማጣት ችግር ገጥሞናል
- የትኩረት መቆራረጥ ችግር ገጥሞናል
- ትዕግሥት የማጣት ችግር ገጥሞናል
- ጥድፊያና አለመረጋጋት ገጥሞናል
- የትም የምንሄድበት ባይኖረንም እንቸኩላለን

# የማኅበራዊ ሚድያው አሉታዊ ነገሮች

## እንደ ወንጌል አማኝነታችን ስናስብ

- አገልጋዮቻችን እንዳናከብር እያደተደረግን ነው
- ጸጋን የሚያጣጥል ትውልድ እየተነሣ ነው
- መንፈሳዊ ፋይዳ ያላቸው ልምምዶቻችን ቀለው እንዲታዩን እያደረገን ነው

# የማኅበራዊ ሚድያው ሱስ ዋና ዋና ጉዳቶች

በርካታ ጨዋ አማኞች ተሰናክለዋል

- ተሳዳቢ ሆነዋል
- ማንምም የማይሰሙ ሆነዋል
- ሸቅብ ወደ ላይ እየተንጠራሩ መሪዎችን የሚዘልፉ ሆነዋል
- እኔ ብቻ አዋቂ ነኝ የሚሉ ሆነዋል

# የማኅበራዊ ሚድያው ዘገባ ግነትና አደጋ!



# የማኅበራዊ ሚድያው ዘገባ ግነትና አደጋ!



# የማኅበራዊ ሚድያው ሱስ ዋና ዋና ጉዳቶች

ማንነታችንን ለዓለም ፍንትው አድርጎ አሳይቷል

- የወንጌል እውነት እንዳልገባን
- ደቀ መዝሙርነት ላይ እንዳልሠራን
- በውስጣችን ሸሽገን የያዝናቸው ብዙ ነውሮች እንደነበሩን

*ለምሳሌ ዘረኝነት*

*አክራሪነት*

*አላዋቂነት*

*ገንዘብ ወዳድነት*

# ደቀ መዝሙርነት ላይ እንዳልሠራን




@ Ev

# መፍትሔ

ችግሩ የቱንም ያህል አሳሳቢ ቢሆንም መፍትሔ የሌለው ግን አይደለም

# ስለዚህ አጠቃቃማችንን እናስተካክል

- ከእግዚአብሔር ይልቅ ስፍራ የምሰጠው ነገር ሁሉ ጣኦት ነው
- ከውጪ ያለ እርሱ መኖር እንደማንችል የሚሰማን ነገር ሁሉ ኃጢአት ነው
- ስልኮቻችንን ታብሌቶቻችንን በዚህ መልክ የምናመልካቸው ከሆነ አደጋ ላይ ነን
- ማለዳ ስንነሳ፣ ማታም ስንተኛ ስልኮቻችንን ቀድመው ትዝ የሚሉን ከሆነ አደጋ ላይ ነን

# የት ጋር እንዳለ መርምሮ መረዳት

## ራእ.2፥5

እንግዲህ ከወዴት እንደ ወደቅህ አስብ ንስሐም ግባ የቀደመውንም ሥራህን አድርግ፤ አለዚያ እመጣብሃለሁ ንስሐም ባትገባ መቅረዝህን ከስፍራው እወስዳለሁ።

# እንግዲህ ከወዴት እንደ ወደቅህ አስብ



# የት ጋር እንዳለ መርምሮ መረዳት

- በዚህ ያለን ሁላችን የማኅበራዊ ሚድያ አጠቃቀማችን የተለያየ እንደሚሆን የታወቀ ነው

- በመሆኑም የመጀመሪያ እርምጃ የት ጋ ነኝ የሚለውን ማወቅና መረዳት ነው

- ራስን ለመከላከል መሞከር መፍትሔ ላይ አያደርስም

# ለማኅበራዊ ሚድያ ግንኙነታችን ገደብ ማበጀት

- ለምሳሌ የማኅበራዊ ሚድያ ፆም ማወጅ
- በዚህም ለሆነ ጊዜ ተለይተን መቆየት መቻላችንን ማረጋገጥ
- በተቻለ መጠን ማታ ማታ ስልካችንን ከእኛ አርቀን መተኛት

# የሚጠቅሙ እና የማይጠቅሙ ነገሮችን መለየት

- ይህ ነገር በሕይወቴ የሚሰጠኝ ጥቅም ምንድን ነው?

- አንዳንድ ሰዎችን፣ ወይም ፕሮግራሞችን ዴሊት ማድረግ

ለምሳሌ፣ የዘር ጥላቻን የሚሰብክ፣

የማይረባ ነገር የሚናገር፣

ዖታዊ ንጽሕና የሌለው

# ሶሻል ሚድያው የሚጠቀምብን ሳይሆን የምንጠቀምበትን ዕድል መጠቀም

ለምሳሌ

- ለወንጌል ስርጭት
- ለንግድ
- ሌሎችን ለማንቃትና
- ለማስተማር

# በሌሎች ጠቃሚ በሆኑ ጉዳዮች ላይ ማተኮር

- የሙያ ሥልጠናዎች

  ለምሳሌ

  ልዩ ልዩ ሙያና

  ልዩ ልዩቴክኒክ ለመማር

- ስብከት እና ትምህርቶችን ለመስማት

# ዕድለኛ ማለት

አልጋዉ አጠገብ ቻርጀር
ያለዉ ሰዉ ነዉ።



# የበሽተኞች ዓለም ይሆን?

- አንድ ጥናት በማኅበራዊ ሚድያ ዋነኛ ተሳታፊዎች መኻል አብዛሻዎቹ የአእምሮ በሽተኞች እንደ ሆኑ አረጋግጧል

- ማኅበራዊ ሚድያው፣፣ በጤነኛው ማኅበረሰብ ያጡት ተቀባይነት ያገኙ ሰዎች መደበቂያ ሆኗል ተብሎ ይጠረጠራል

- ተሳዳቢ ሰዎች የተከማቹበት፣
- ጠብ ጫሪ ሰዎች የሞሉበት፣
- መረን የወጡ ስድ ነገሮች የሚሰሙበት

# የክፉ ተጽእኖ እንዳለ አንርሳ



# እነዚህን ነገሮች ብናደርግስ

1ኛ፡ የማበራዊ ሚድያ አጠቃቀማችን በቤተ ክርስቲያን ተጠያቂነት ያለው እንዲሆን ብንፈቅድ፣

2ኛ፡ ከዚህ ቀን በኋላ ከስልካችን የምንፆምበት ጊዜ ቢኖረን፣

3ኛ፡ ቤተ ክርስቲያን ስንመጣ ስልካችንን የመዝጋት ባህል ቢኖረን፣

4ኛ፡ መጽሐፍ ቅዱስ በሀርድ ኮፒ የመጠቀም ልማድ ብናዳብር፣

# እነዚህን ነገሮች ብናደርግስ






# መጽሐፍ ቅዱስ በሞባይል ብንጠቀም ችግሩ ምንድን ነው?

በስልካችን ስንጠቀም ብዙ መረበሽ ይደርስብናል

መልእክት ይገባል

ስልክ ይደወልልናል

የማኅበራዊ ሚድያው ላይ ያሉ ገጾቻችን ውስጥ የሚተላለፈው ይስበናል

. . .

በዚያ ላይ ሶፍት ኮፒው መጽሐፍ ቅዱስ ለመጭበርበር የተጋለጠ ነው

# ወደ ቤተ ክርስቲያን ስንመጣ . . .



# ማጠቃለያ

- <u>ወደ ቤት እንግባ፤ ደጃችንን እንዝጋ፤ እንሸሸግ</u>

ኢሳ.26:12፤

*አቤቱ፥ ሥራችንን ሁሉ ሠርተህልናልና ሰላምን ትሰጠናለህ።*

ኢሳ.26:13፤

*አቤቱ አምላካችን ሆይ፥ ከአንተ በቀር ሌሎች <u>ጌቶች ገዝተውናል፤</u> ነገር ግን በአንተ ብቻ ስምህን እናስባለን።*

-

# ማጠቃለያ

ኢሳ.26:20፤

*ሕዝቤ ሆይ፥ ና ወደ ቤትህም ግባ፥*

*ደጅህን በኋላህ ዝጋ*

*ቍጣ እስኪያልፍ ድረስ ጥቂት ጊዜ ተሸሸግ።*